# ባንዳ ልብ ግዛ!




ውርደት ሆዳምነት ቢመዘን ቢለካ፣
ከይሁዳ ሳጥናኤል ተጭራቅ የከፋ፣
ባንዳ እንደ አንተ አለ ወይ እጅግ የከረፋ?

ከርስህን አስፍተህ እንደ ስንዴ ኬሻ፣
ጅራትህን ወትፈህ ተጭራቆች ጉያ፣
ወገን አታስነክስ ባንዳ ልብ ግዛ!

መሞት ላይቀርልህ በእድሜ በበሽታ፣
መብል አስጎምጅቶህ የባሰም ተአሳማ፣
ወገንህን ለሚያርዱት አትሁን እጀታ፣
እስቲ አሞት ይኑርህ ባንዳ ልብ ግዛ፡፡

የምትኖራት እድሜ ሰማንያ ላትሞላ፣
ታሪክ አይርገምህ ዘላለም ጧት ማታ፣
ተው ንስሀ ግባ አቁም! ይብቃህ! ባንዳ!

ከምሳር እጀታ ከዛቢያውም ከፍተህ፣
ህጻናት ተሚያርዱት ቂጥህን ወትፈህ፣
ዘመድ ወገንህን ያሳጨድክ ያስቆረጥክ፣
ምድር ተሰንጥቃ ወደ ውስጥ ታስምጥህ፣
ሰማይ ቋያ ሆኖ እንደ እሳት ያንድህ!

እንደ አምስቱ ዘመን እንደ አድዋው ባንዳ!
ሞተህ እንደ አህያ ነገ ልጠነባ፣
ምስጥ እንክት ሊያደርግህ እስክትሆን ትቢያ፣
ጭራቅ ሎሌው አርጎህ ወገን አታስበላ፣
ተመከር ተዘከር ባንዳ ልብ ግዛ፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)

ሐምሌ ሁለት ሺ አስራ አምስት ዓ.ም.